# የፌደራል ስፖርት ልማት እና አስተዳደር አዋጅ መግለጫ

## መግቢያ

ስፖርት ማንኛውም ሰው በግሉ ወይም በጋራ በተደራጀ ወይም ባልተደራጀ ሁኔታ የሚያከናውነው እንቅስቃሴ ሲሆን ጤንነትን ለመጠበቅ፣ ለመዝናናት፣ አካልን ለመገንባትና አዕምሮውን ለማበልፀግ ያገለግላል፡፡ በዚህም ዘርፉ ንቁና ጤናማ ትውልድ በማፍራት ተወዳዳሪና አሸናፊ ሀገርን ለመገንባት ያለውን ሚና በተገቢው እንዲወጣ ያለው ሚና እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህም ስፖርት ከተለመደው አካላዊ እንቅስቃሴ እና ጨዋታ ባለፈ ለሀገር ልማት፣ ለሰላም ግንባታ፣ ለማህበራዊ ትስስር፣ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገትና ለድህነት ቅነሳ መርሃ ግብሮች፣ ጠንካራ ሀገር ለመገንባትና ዓለም አቀፍ ግንኙነቶችን ለማጠናከር ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ ስለሆነም ዘርፉ ካለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ በመረዳት ሀገራት ተገቢውን ትኩረት በመስጠት እና የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት በኢንዱስትሪ ደረጃ በማደራጀት እየተገለገሉበት ይገኛሉ፡፡

በኢትዮጵያ ዘመናዊ ስፖርት ከመጀመሩ በፊት ህብረተሰቡ በተለያዩ የባህል ስፖርት አይነቶች ይሳተፍ ነበር፡፡ ዘመናዊ ስፖርት በሀገራችን ከተስፋፋ በኃላም በርካታ ክለቦችና ስፖርተኞች በማፍራት በዓለም አቀፍ መድረኮች ተፎካካሪና አሸናፊ ሀገር ለመሆን ተችሏል፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ የሀገራችን የስፖርት እንቅስቃሴ እየተሻሻለ በመምጣቱ እና የዘርፉን ሁለንተናዊ ፋይዳ በመገንዘብ የተለያዩ ብሔራዊ የስፖርት ተቋማትና ማህበራት ተመስርተው ስራ ላይ እንዲውሉ ከመደረጉም በላይ በሰው ኃይል ልማትም ፈርጀ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 41 ንዑስ ቁጥር 9 መንግስት ስፖርትን የማስፋፋት ኃላፊነት እንዳለው ተደንግጓል፡፡ ይህንን ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌ ለማስፈጸም በ1990 ዓ.ም የስፖርት ፖሊሲን በመቅረጽ ዘርፉ በመንግስታዊና በህዝባዊ አደረጃጀት እንዲዋቀር አስችሏል፡፡ በዚህም መሰረት የተለያዩ የዘርፉ ተቋማትንና የአሰራር ስርዓቶችን መዘርጋት ተችሏል፡፡

ይሁን እንጂ ስፖርት ካለው ዕምቅ ሀብት፣ ከዘርፉ ውስብስብነት እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ አዘምኖ ለመጠቀም ካለው ሀገራዊ ፍላጎት አኳያ ወቅቱን ያገናዘበ ዘመናዊ አሰራር አልተዘረጋም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ያሉት የህግ ማዕቀፎች የተበታተኑና ለአፈጻጸም ምቹ ባለመሆናቸው ዘርፉ ለብልሹ አሰራርና ለመልካም አስተዳደር ችግር የተጋለጠ ሆኗል፡፡ በዚህም ምክንያት ዘርፉ የሚያመነጨውን የሥራ ዕድል፣ በኢንዱስትሪው የሚንቀሳቀሰውን ሀብት እና ያሉትን የኢንቨስትመንት አማራጮች በአግባቡ በመቆጣጠር መጠቀም ባለመቻሉ ዘርፉ በሀገር ግንባታ፣ በስራ ዕድል ፈጠራ፣ በማህበራዊ ልማት እና በአጠቃላይ ሀገራዊ ኢኮኖሚ ሊያበረክት የሚገባውን ጉልህ ሚና ለመጫወት አልቻለም፡፡ ስለሆነም በሀገር አቀፍ ደረጃ ዘርፉን በመምራት ለዘላቂ

ሀገራዊ ልማት ለመጠቀም እንዲያስችል የፌደራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር አዋጅ ተዘጋጅቷል፡፡

## 1. አዋጁን ለማዘጋጀት መነሻ ሆኑ ምክንያቶች

በሀገራችን የስፖርት ልማት ዙሪያ በተደረጉ ጥናቶች ስፖርቱ ብዙ ችግሮች ያሉት መሆኑ ተለይቷል፡፡ እነዚህ ችግሮች በአግባቡ በአሰራር ቢፈቱ የሀገራችን የዘርፉ ልማት በዘላቂነት ለማስቀጠል እድል ይፈጥራል፡፡

ስለዚህም ለዘርፉ ዘመናዊ አሰራር ለመዘርጋት ይህ አዋጅ እንዲዘጋጅ የመነሻ ምክንያቶች እንደሚከተሉት ቀርበዋል፡፡

- ስፖርት በየወቅቱ እያደገ የሚሄድ አለም አቀፋዊ ባህሪ ያለው ዘርፍ በመሆኑ ይህን እድገት የሚመጥን ወቅታዊና የተናበበ ዘመናዊ አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አኳያ የዘርፉ ሀገራዊ አሰራሮች የተበታተኑ፣ ያልተናበቡና ወቅታዊነት የሚጎላቸው ናቸው፡፡ ስለዚህም ዘርፉን ለሀገራዊ ሁለንተናዊ ልማት እንዲውል የሚያግዝ ዘመናዊ አሰራር መዘርጋት አስፈልጓል፡፡
- የስፖርት ልማት የተለያዩ መንግስታዊ፣ የግል ባለሃብቱን እና ንቁ የማህበረሰብ ተሳትፎን የሚጠይቅ ዘርፍ ነው፡፡ይሁን እንጂ ለሀገራዊ ስፖርት ልማት ቅንጅቱን በማዕከልነት ለማስተባበር የሚያስችል ጅምር ተግባራት ቢኖሩም ከወጥነትና ከዘላቂነት አንጻር ክፍተቶች ተስተውለዋል፡፡ በመሆኑም የዘርፉ ልማት ውስብስብ ባህሪ ያለው በመሆኑ የሚመለከታቸውን አካላት አቀናጅቶ ማስተባበርና መምራት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡
- ስፖርት በዓለማችን ላይ እያደገ የመጣ ዘርፍ በመሆኑ ለአንድ አገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚኖረው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአገራችን ስፖርቱ ለኢኮኖሚው ዕድገት፣ ለዜጎች የስራ ዕድል ፈጠራ፣ ለዘርፉ ኢንቨስትምንት እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ በውል የሚታወቅ ካለመሆኑ በተጨማሪ የስፖርት ንግድን የሚያበረታታ ስርዓት አልተፈጠረም ፡፡ በመሆኑም የስፖርት ንግድ ስርዓትን በመዘርጋት የስፖርት ምጣኔ ሀብታዊ አበርክቶ ማሳደግ አስፈልጓል፡፡
- የስፖርት ዘርፍ አደረጃጀቶች ከመንግስትና ከአለም አቀፍ ማህበራት ጋር ያላቸው ግንኙነት በአግባብ በአሰራር አልተለየም፡፡ በዚህም ምክንያት በህዝባዊና በመንግስታዊ

አደረጃጀቶች መካከል ከፍተኛ አለመግባባት በመፈጠሩ በዘላቂ የስፖርት ልማት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም የስፖርት ዘርፍ አደረጃጀቶችን በተገቢው ሁኔታ ለመምራት የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

- በስፖርት ማህበራት መካካል የሚነሱ አለምግባባቶችን እንደአገር የሚፈታበት ስርዓት የለም፤ በዚህም ምክንያት በማህበራት መካከል ለሚፈጠሩ ችግሮች እና በስፖርት ማህበረሰቡ ዘንድ የሚነሱ ጥያቄዎችን መፍታት ባለመቻሉ ከፍተኛ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲኖር ዕድል ፈጥሯል፡፡ በመሆኑም  በስፖርት ማህበራት ውስጣዊ አሠራርና በማሕበራት መካካል ያለው አለመግባባት ለመፍታተ፣የአማተር አመራሩና የሕዝባዊ አሰራር ተገቢነት እና የመንግስት የቁጥጥር እና የፍትህ አካላትን ተሳትፎ የሚያጎላ አሠራር ያስፈልጋል፡፡
- የስፖርት ልማት ከፍተኛ መዋለንዋይ የሚፈልግ ነው፡፡ በመሆኑም የአገራችን ስፖርቱ በመንግስት ድጋፍ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በሚፈለገው ደረጃ ስፖርቱን በማሳደግ በዓለም አቀፍ ደረጃ በሁሉም ስፖርት ተወዳዳሪ ለመሆን አልተቻለም፣ ስለሆነም መንግስት ከሚሰጠው ድጋፍ በተጨማሪ ስፖርቱ የራሱን ገቢ ማመንጨት እንደሚገባው የፖሊሲ አቅጣጫና የሚኒስቴሩም ተግባርና ኃላፊነት በመሆኑ ተጨማሪ የገቢ ምንጮችን በመፍጠር ለዘላቂ የዘርፍ ልማት የሚውል የፈንድ አሠራር መቅረጽ ያስፈልጋል፡፡
- አገራችን በውስን ስፖርት ዓይነቶች በአለም አቀፍ ደረጃ መልካም ስም መገንባቷ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በተለያዩ ጊዜያት በአትሌቶች በስፖርት ውድድር የበላይነትን ለማግኘት በሚደረግ ፉክክር  አበረታች ቅመሞችንና ዘዴዎችን የመጠቀም አዝማሚያ ተስተውሏል፡፡ በሂደቱም ተሳታፊ የሆኑ አካላትን በአግባቡ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ጠንካራ ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ የስፖርት ማህበራት አስተዳዳርና አመራር ግልጸነትንና ተጠያቂነትን የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው:: በአገራችን ይህን የሚያሰፍን ተገቢው አሠራር ባለመኖሩ በየወቅቱ ላልተገባ አለመግባባቶች አጋልጧል፡፡ ስለዚህም የስፖርት ማህበራት አስተዳደር በስፖርት መርህ መሰረት ግልጸኝነትንና ተጠያቂነት የሚያሰፍን ጠንካራ ስርዓት መቅረጽ ተገቢ ነው፡፡

## 2. የአዋጁ አስፈላጊነት

የስፖርት ዘርፍ ካለዉ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ፋይዳ እንዲሁም አስተዳደራዊ ውስብስብነት አንጻር በአግባቡ መምራትና መቆጣጠር ያስፈልጋል፡፡ የዘርፉ ልማት በርካታ ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት እና ሰፋ ያለ የእሴት ሰንሰለት ያለው በመሆኑ ዘመናዊ፣ አሳታፊና አካታች የሆነ የህግ ማዕቀፍና አስተዳደራዊ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ተገቢ ነው፡፡

ይህ አዋጅ ጸድቆ ተፈጻሚ ሲሆን ሁለንተናዊ ፋይዳው የጎላ እንደሚሆን ይጠበቃል፡፡ በተለይም የስፖርት ኢንቨስትመንትን በማበረታታት፣ ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት መሰረተ ልማቶችን በማስፋፋት፣ በሀገር ውስጥ የስፖርት ግብዓቶችን በማምረትና በማሰራጨት፣ የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማትን በመገንባት እንዲሁም የስፖርት ኩነት አዘጋጅ ድርጅቶችን በማስፋፋት ለዜጎች ከፍተኛ የስራ እድል ይፈጥራል፡፡በተጨማሪም ተተኪና ምርጥ ስፖርተኞችን በማፍራት፣ የዘርፉን አለም አቀፋዊ ተሳትፎ በማጎልበትና ሀገራዊ የስፖርት ብራንዲንግን በመተግበር የውጭ ምንዛሪን ያስገኛል፡፡ ይህም ሀገራዊ ኢኮኖሚ ላይ አዎንታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል፡፡

በሌላ በኩል ስፖርት ለማህበራዊ ልማት የማይተካ ሚና ያለው ዘርፍ ሲሆን ጤናማና ንቁ ዜጋ በመፍጠር፣ በዜጎች መካከል ማህበራዊ ትስስርን በማጎልበት እንዲሁም ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነትን ለማጠናከር የሚያገለግል ጉልህ ሚና ያለው ነው፡፡

ስለሆነም የሀገራችንን ዘላቂ የስፖርት ልማት አስተባብሮ በመምራት የሚከተሉትን ውጤቶች ለማግኘት ይህን አዋጅ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡

- ህብረተሰቡ በአካላዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ጤናማ፣ ንቁና አሸናፊ ሀገር መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤
- የስፖርት ዘርፉን ሃብቶች በማልማትና በማስተዋወቅ ሀገራዊ የዘርፉ ኢንቨስትመንትና የስራ እድሎችን በማስፋፋት ምጣኔ ሀብታዊ አስተዋጽኦውን ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤
- ለስፖርት መሰረተ ልማት ግንባታዎች፣ ማዘውተሪያ ስፍራዎችና ቁሳቁሶች ተገቢውን የአስተዳደርና የአጠቃቀም ስርዓት መዘርጋት ለዘላቂ የስፖርት ዕድገት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤
- የስፖርት ተቋማት የግንኙነት አግባብ በመርህ ላይ የተመረኮዘ በማድረግ በዘርፉ የሚነሱ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት በማስፈለጉ፤

- ስፖርት በአለም አቀፍ ደረጃ የደረሰበትን የእድገት ልክ የሚመጥን ዘመናዊና ተናባቢ፣ ወጥ፣ ፍትሐዊና ግልፅ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤
- መንግስት ስፖርትን ለማስፋፋት የሚሰጠው የድጋፍ ማዕቀፍ በዘርፉ ውጤት ለሚያስመዘግቡና በእምቅ ሃብትነት ለተለዩ መስኮች እንዲመደብ የሚያስችል አሰራር መፍጠር በማስፈለጉ፤
- ስፖርት ነክ ወንጀሎችን በመከላከልና ንጹህ ስፖርትን በማስፋፋት ዘርፉ ለሀገር ገጽታ ግንባታ እያበረከተ ያለውን ሚና ማስቀጠል በማስፈለጉ፤

## 3. <u>የአዋጁ አዘገጃጀት ሂደት</u>

መንግስት በ2012 ዓ.ም የስፖርት ልማትን ለማሳለጥ የሚያገለግል ሀገራዊ የስፖርት ሪፎርም ፕሮግራም የቀረጸ ሲሆን በሰነዱም በርካታ የስፖርት ልማት ተግዳሮቶችን ለመለየት ተችሏል፡፡ ከነዚህ ውስጥም አንዱ በዘርፉ የተዘረጉት የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎች እና ስታንዳርዶች ያልተናበቡ በመሆናቸው የተፈለገውን ውጤት እንዳላመጡ ተመላክቷል፡፡ እነዚህን የአሰራር ችግሮች ለመፍታትም የስፖርት አዋጅ መዘጋጀት እንዳለበት እንደ ምክረ ሀሳብ ቀርቧል፡፡

በሚኒስቴሩ ከስፖርት እና ከህግ ዘርፍ ባለሙያዎች የተውጣጡበት ኮሚቴ በማዋቀር ስራው እንዲጀመር ተደርጓል፡፡ በስፖርት ረቂቅ አዋጅ ዝግጅትም የሪፎርም ሰነዱ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሰሩ የዘርፉ ሰነዶች እና የዳሰሳ ጥናቶች እንዲሁም የተለያዩ አገራት ተሞክሮ በመነሻነት ተፈትሿል፡፡ በተለይም ስፖርትን ለገጽታ ግንባታ እና ለኢኮኖሚ ዕድገት የተጠቀሙ የአውሮፓ፣ የደቡብ አሜሪካ እና የአፍሪካ ሀገራት ልምድ ተቀምሮ በአዋጁ ተካቷል፡፡
በዝግጅቱም ሀገራዊ የዘርፉ የአሰራር ስርዓቶች፣ መመሪያዎች እና በስራ ላይ የነበሩ የህግ ማዕቀፎች ተፈትሸው ክፍተታቸው እንዲለይ ተደርጓል፡፡ የነዚህ ሰነዶች አጠቃላይ ይዘትን በመውሰድ፣ አዳዲስ ወቅታዊ አስተሳሰቦችን በማካተት እና ለተለዩ ችግሮች ተገቢ የመፍትሔ ሀሳቦች ተለይተው ሰነዱ እንዲዳብር ተደርጓል፡፡ በተለይም ስፖርት እንደ ኢንዱስትሪ እንዲለማ ተገቢነት ያላቸው ሀገራዊ ተሞክሮዎች አግባብነታቸው የተመረመረ ሲሆን አማራጭ የሆኑ ገንቢ ሃሳቦች ተወስደው በሰነዱ ተካተዋል፡፡ በአጠቃላይ በአዋጁ ዝግጅት ወቅት ዘላቂ የዘርፉን ልማት የሚያረጋግጡ በዘርፉ የዜጎችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ የሚያጎለብቱ ሃሳቦችና ተሞክሮዎች ከሀገራዊ ሁኔታዎች ጋር በማጣጣም በሰነዱ ተካተዋል፡፡

## 4. <u>የባለድርሻ አካላት ውይይት እና የተሰጡ አስተያየቶች</u>

በዚህ የአዋጅ ዝግጅት ወቅት የሚመለከታቸው አካላት በተለያዩ ጊዜያት ውይይት እንዲያደርጉበት ተደርጓል፡፡ በተለይም በዘርፉ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራን በተደጋጋሚ ጊዜያት ውይይት በማድረግ ሰነዱን የሚያዳበሩ አስተያየቶች አቅርበዋል፡፡ ይህም የስፖርት ልማትና አስተዳደርን በሚመለከት የመንግስት የጣልቃ ገብነት ድርሻ እንዲኖረውና አዋጁ በተወሰነ መልኩ ሃሳቡን እንዲያስተናግድ አቅርበዋል፡፡

በሌላ በኩል የአገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ስራ አስፈጻሚዎች በአዋጁ ላይ ተደጋጋሚ አስተያየቶች ያቀረቡ ሲሆን ይህም ከአገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት አስተዳደር፣ ምዝገባ እና የአመራሮችን የአገልግሎት ዘመንን በሚመለከት አስተያየቶች አቅርበዋል፡፡ በተለይም በተጠሪነት፣ ከመንግስት የድጋፍ ስርዓት እና ከአለም አቀፍ ተሳትፎ እንዲሁም ከብሄራዊ ቡድን ዝግጅት አኳያ ሃሳብ ያቀረቡ ሲሆን አዋጁም እንደነገሩ አግባብነት በማዳበሪያነት ተጠቅሟል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የአትሌት ተወካዮች፣ የዳኞች ተወካዮች፣ ኮሚሽነሮች፣ በዘርፉ ላይ ከተሰማሩ ባለሙያዎች እና በክልል የዘርፉ አመራሮች ጋር ተደጋጋሚ ውይይት በማድረግ የተለያዩ ገንቢ አስተያየቶች ተሰጥቶበታል፡፡ በመጨረሻም የስፖርት አስተዳደር አዋጁ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ አመራር እና ተጠሪ ተቋማት አመራሮች፣ ለዘርፉ ቋሚ ኮሚቴ አባላት እና ለባለድርሻ አካላት ቀርቦ ውይይትና ግብዓት ተሰጥቶበት እንዲዳብር ተደርጓል፡፡

## 5. <u>አጠቃላይ የስፖርት አስተዳደር አዋጅ ሰነድ ላይ የተነሱ ዋና ዋና አስተያየቶች እና ሃሳቦች</u>

- ✓ ከዘርፉ ስፋትና ጥልቀት የተነሳ ዘርፉን ለመምራት እና ለማስተዳደር፣ የስፖርት ማህበራት ስለሚቋቋሙበትና ስለሚተዳደሩበት ሁኔታ፤ የዜግነት ጉዳይን እና የአገር አቀፍ ስፖርት ማህበራት ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ የስራ ዘመን የሚመለከት በመመሪያ ብቻ መወሰን የለበትም በአዋጁም ቢካተት የሚል ሀሳብ ተነስቷል፤
- ✓ በአሰልጣኞች፣ ማናጀሮችና በአትሌት ተወካዮች መካከል በሚደረግ የጥቅም ግጭት አገሪቱን እንዳይጎዳ እነዚህ አካላት ሊዳኙበት የሚችሉ አንቀጽ ቢቀመጥ፤
- ✓ የውጭ ሀገር ስፖርተኞችን ስለመቅጠር የተቀመጠው ሁኔታ ታይቶ የውጭ ሀገር ባለሙያ መቅጠርን በሚመለከት በአገሪቱ ውስጥ ባለሙያ አለመኖሩ ሲረጋገጥ መቀጠር እንዳለበት ለዚህም አረጋጋጭ አካል ቢቋቋም፤

- ✓ የስፖርቱ አጠቃላይ አስተዳደር ከአማተሪዝም ወደ ፕሮፌሽናልዝም (የስፖርት ሳይንስ ባለሙያዎች) የተሻለ ድርሻ እንዲኖራቸው ቢደረግ፡፡
- ✓ የስፖርት ውርርድ ጉዳትና ጥቅሙ በጥናት ተለይቶ የአገሪቱን ስፖርት ልማት በማይጎዳ መልኩ የቁጥጥር ስርዓት ቢዘረጋለት፤
- ✓ የመንግስት ድጎማ በምን አግባብ እንደሆነ እና የስፖርት ማህበራት ኦዲት ለማድረግ፣ ስለብሔራዊ ስፖርት ሙዚየም አንድ አንቀጽ ቢካተት በማለት አስተያየት ተሰጥቷል፡፡

  ከላይ የተጠቀሱት እና ሌሎች በአዋጁ ላይ የተነሱ ሃሳቦች እንደአግባብነታቸው በግብዓትነት እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

## 6. የተወሰዱ ተሞክሮዎች

በስፖርት አስተዳደር አዋጅ ዝግጅትም የስፖርት ሪፎርም ሰነዱ፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሰሩ የዘርፉ ጥናቶች እና የዳሰሳ ጥናቶች እንዲሁም የተለያዩ አገራት ተሞክሮ በመነሻነት ተፈትሿል፡፡ በተለይም ስፖርትን ለገጽታ ግንባት እና ለኢኮኖሚ ዕድገት የተጠቀሙ የአውሮፓ፣ የደቡብ አሜሪካ እና የአፍሪካ አገራት ልምድ ተቀምሮ በአዋጁ ተካቷል፡፡
ከአትሌቶችና የስፖርት ባለሙያዎች ምልመላ፣ መረጣ፣ የብሔራዊ ቡድን አመራር፣ ከመንግስት አካላት ድርሻ አኳያ እና ከማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር እና ልማት አንፃር የራሺያ፣ ክሮሺያ፣ እንግሊዝ እና ብራዚል ልምድ ተወስዷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ከኬኒያና ደቡብ አፍሪካ እንዲሁም ናይጀሪያ መንግስት በስፖርት ዘርፍ የሚኖረውን የድጋፍ አግባብ የአስፈላጊነቱን ደረጃ በመለየት በአዋጁ ተካቷል፡፡

## 7. የአዋጁ አደረጃጀት

አዋጁ  በአስር ክፍሎች በአስራ አንድ ንዑስ ክፍሎች የተዋቀረ ነው፡፡

## 8. ማጠቃለያ

ይህ አዋጅ ተዘጋጅቶ በሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ውይይት ከተደረገበት በኋላ ለኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፍትህ ሚኒስቴር ለሁለት ጊዜያት ተልኳል፡፡ በዚህም ፍትህ ሚኒስቴር ለሁለት ጊዜያት በሰነዱ ላይ ተገቢውን አስተያየት በተለይም በሁለተኛው ዙር የተሰጠው አስተያየት ሰነዱን ለማዳበር ከመጥቀሙም በላይ በአዋጁ አፈጻጸም የሚመለከታቸው አካላት ድርሻ እንዲመላከት በብዙ ደግፏል፡፡ አስተያየቱ ከአዋጁ ቅርጽ ባለፈ በአገላለጽ፣ በአዋጁ ህገ-መንግስታዊነት፣ ከአስተዳደራዊ አመቺነት አንጻርና ከዘርፉ አስተዳደር አኳያ ሰፊና ገንቢ ሃሳቦች አካቷል፡፡

በዚህም ሙያዊ የሆነው የዘርፍ አስተዳደር ጉዳይ በነበረበት በማሻሻል ሌሎች አስተያየቶችን በገንቢነት በአዋጁ ተካቷል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም የሀገራችን የህግ አወጣጥ ስርዓቶችን በመከተል አጠቃላይ የአዋጁ ቅርፅ እንደ አዲስ ተቀርጿል፡፡ በአጠቃላይ በባለድርሻ አካላት እና በፍትህ ሚኒስቴር በተሰጡ አስተያቶች ዳብሮ የተዘጋጀውን የስፖርት አዋጅ እና የአዋጁ መግለጫ ተዘጋጅቶ ቀርቧል፡፡

## አዋጅ ቁጥር ... /2018 ዓ.ም

## የፌደራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር አዋጅ

ማንኛውም ሰው በሚኖርበት፣ በሚሰራበት፣ በሚማርበት እና በሚዝናናበት አካባቢ እንደፍላጎቱና እንደችሎታው በግል፣ በቡድን በተደራጀና ባልተደራጀ መልኩ በአካላዊ እንቅስቃሴ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆን በማድረግ ጤናማና ንቁ ዜጋ፣ አሸናፊ አገር መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤አገር አቀፍ ስፖርት ማህበር

የስፖርት ዘርፍንና እምቅ ሃብቶቹን በማልማትና በማስተዋወቅ ሀገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘውን ሁለንተናዊ ጥቅም ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና ቁሳቁሶች ተገቢውን የአስተዳደርና አጠቃቀም ስርዓት በመዘርጋት ማህበረሰቡ በስፖርት እንቅስቃሴዎች ለመሳተፍና ተጠቃሚ ለመሆን ያለውን መብት ማረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የስፖርት መረጃን በተገቢው በመያዝና ተደራሽ በማድረግ ለዘርፉ ሁለንተናዊ ልማት አስፈላጊውን ሚና እንዲያበረክት በማስፈለጉ፤

የስፖርት ዘርፍ የሚመራበትንና የሚተዳደርበትን ወጥ፣ ፍትሐዊና ግልፅ የአሠራር ስርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት በአንቀፅ 55 ንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "**የፌደራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር .... /2018**" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ **“ስፖርት”** ማለት ማንኛውም ሰው ጤንነቱን ለመጠበቅ፣ ለመዝናናት፣ አካሉን ለመገንባትና አዕምሮን ለማበልፀግ እንዲሁም አቅሙንና ችሎታውን ለመመዘን

በግሉ ወይም በቡድን በተደራጀ ወይም ባልተደራጀ ሁኔታ የሚከናወን እንቅስቃሴ ነው፤

2/ **"ስፖርታዊ እንቅስቃሴ"** ማለት ማንኛውም ስፖርታዊ ጨዋታ፣ ውድድር፣ ልምምድና ሥልጠናን ይጨምራል፤

3/ **"የስፖርት ኩነት"** ማለት ስፖርታዊ እንቅስቃሴ፣ መዝናኛ ፣ ፌስቲቫል፣ ስብሰባ፣ ሴሚናር፣ ሲንፖዚየም፣ ኮንፈረንስ እና ወርክሾፕን ያጠቃልላል፤

4/ **"የስፖርት ልማት"** ማለት ስፖርትን በዘላቂነትና በሁለንተናዊነት ለማሳደግ የሚከናወን ማንኛውም ተግባር ነው፤

5/ **"የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ"** ማለት ለስፖርታዊ ኩነት ማከናወኛነት እንዲውል የተዘጋጀ ቦታ ነው፤

6/ **"የስፖርት ትጥቅና መሳሪያ"** ማለት ስፖርታዊ እንቅስቃሴን ለማከናወን የሚያገለግል ትጥቅ እና መሳሪያ ነው፤

7/ **"አትሌት"** ማለት በመደበኛ ስልጠና በመታገዝ በስፖርታዊ ውድድር ወይም ጨዋታ ላይ የሚሳተፍ ሰው ነው፤

8/ **"ብሔራዊ ቡድን"** ማለት ሀገርን በመወከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ስፖርታዊ ውድድሮች ወይም ጨዋታዎች ላይ የሚሳተፍ ስብስብ ነው፤

9/ **"የስፖርት ባለሙያ"** ማለት በስፖርት ሙያ መስክ በመሰልጠን እና ባለው ክህሎት ለመስራት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለው ሰው ነው፤

10/ **"የፌደራል የስፖርት ማህበር"** ማለት አንድን የስፖርት ዓይነት ወይም የተለያዩ የስፖርት ዓይነቶችን በአገሪቱ ለማስፋፋትና ለመምራት በሚኒስቴሩ ተመዝግቦ ፈቃድ ያገኘ አደረጃጀት ነው፤

11/ **"አለም አቀፍ ውድድር ወይም ጨዋታ"** ማለት በሀገራት፣ በክፍለ አህጉር፣ በአህጉር ወይም በአለም አቀፍ ደረጃ የሚከናወን የስፖርት ውድድር ወይም ጨዋታ ነው፤

12/ **"አለም አቀፍ ስፖርት ማህበር"** ማለት በስፖርት አይነት በአለም አቀፍ ደረጃ የተደራጀ ማህበር ነው፤

13/ **"የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋም"** ማለት ተተኪና አትሌቶችን ወይም የስፖርት ባለሙያ ለማፍራት የሚቋቋም ኢንስቲትዩት፣ አካዳሚ ወይም ማዕከል ነው፤

14/ **"ስፖርት ንግድ"** ማለት የስፖርት ኩነት ማዘጋጀት፣ ተተኪና ውጤታማ ስፖርተኞች በማፍራት ማዘዋወር፣ በክለብና በአትሌቶች ዝውውር መስማራት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ማስተዳደርና ማስፋፋት፣ የስፖርት ትጥቆችና መሳሪያዎች ማምረት ወይም ከውጭ ሀገር ማስገባት ወይም ማከፋፈል፣ የጂምናዚየም አገልግሎቶችን መስጠት፣ በዘርፉ ማማከር፣ ማሰልጠን እና የምርምር ስራዎችን የማከናወን አገልግሎቶችን ያካትታል፤

15/ **"አበረታች ቅመሞች"** ማለት በዓለም አቀፍ የፀረ አበረታች ቅመሞች ህግጋት ለአትሌት የተከለከለ ማንኛውም ንጥረ ነገር ወይም ዘዴ ነው፤

16/ **"የመሰናዶ ስራ"** ማለት ማንኛውም ሰው ለደንበኞች አገልግሎት መስጠት ከመጀመሩ በፊት የሚያከናውነው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራን የመገንባት ወይም ሌላ ግንባታን ወደ ስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራነት የመለወጥ እና አስፈላጊ የስፖርት ትጥቆችንና መሣሪያዎችን የማሟላት ሂደት ነው፤

17/ **"የአትሌት ማናጀር ወይም ተወካይ"** ማለት የአትሌቱን የስልጠና ስርዓት በመደገፍ በዓለም አቀፍ ውድድር እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ሰው ነው፤

18/ **"ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር"** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

19/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ ከተማና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

20/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ ሰውነት የተሰጠው አካል ነው፤

21/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር የሴት ጾታን ይጨምራል፤

## 3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ደረጃ በሚከናወኑ ማንኛውም የስፖርት ልማት እና አስተዳደር ስራዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## 4. <u>የስፖርት መርሆች</u>

ማንኛውም የስፖርት ልማት እና አስተዳደር በሚከተሉት መርሆዎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡-

1/ የስፖርት ተደራሽነት፤

2/ በስፖርት ሁለንተናዊ መስተጋብር፤

3/ የዜጎች ተሳትፎና ተወዳዳሪነት፤

4/ አጋርነትና ቅንጅታዊ አሰራር፤

5/ ፍትሃዊነት እና አካታችነት፤

6/ ግልጸኝነትና ተጠያቂነት፤

## ክፍል ሁለት
## የስፖርት ተቋማትን ስለማቋቋምና ስለማስተዳደር
## ንዑስ ክፍል አንድ
## የፌደራል የስፖርት ምክር ቤት ስለማቋቋም

5. **መቋቋም**

የፌዴራል የስፖርት ምክር ቤት ከዚህ በኋላ "**ምክር ቤት**" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሚል።

6. **የምክር ቤቱ ዓላማ**

በሀገሪቱ የስፖርት ዘርፍ የሚስተዋሉ የአሠራር ማነቆዎችን በባለድርሻ አካላት ቅንጅት በመፍታት የስፖርት ልማትን እና ውጤታማ አስተዳደርን ማረጋገጥ ነው።

7. **የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1/ የስፖርት መሰረተ ልማት ስለሚስፋፋበት ሁኔታ ይመክራል፤ አቅጣጫ ይሰጣል፤

2/ ስፖርት ህዝባዊ መሰረት እንዲኖረው በሚያደርጉ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፤ አቅጣጫ ይሰጣል።

3/ በስፖርት ማህበራት አመራር የሚነሱ አለመግባባቶች የሚፈቱበትን አግባብ ይቀይሳል፤ ተገቢውን አቅጣጫ ይሰጣል።

4/ ሌሎች ከዓላማው ጋር በሚዛመዱ ጉዳዮች ላይ ይመክራል፣ አቅጣጫ ይሰጣል።

8. **የምክር ቤቱ አባላት**

1/ ምክር ቤቱ አባላቱና ቁጥሩ በሚኒስቴሩ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወሰን አባላት የሚኖሩት ሆኖ

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ……………………………………………………… ሰብሳቢ

ለ) ሚኒስትሩ………………………………………………………ምክትል ሰብሳቢ

ሐ) የሚኒስቴሩ የስፖርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ……………………. ጸሀፊ፤ይሆናሉ

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የምክር ቤቱ ሰብሳቢ እንደአስፈላጊነቱ ለስፖርት ዘርፍ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ታዋቂ ግለሰቦችን ወይም ባለሙያዎችን በስብሰባው እንዲሳተፉ ሊጋብዝ ይችላል፡፡

## 9. የምክር ቤቱ ስብሰባ

1/ ምክር ቤቱ በዓመት ሁለት ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፤ ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሰብሳቢው ጥሪ በማንኛውም ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡

3/ የምክር ቤቱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጽ እኩል በእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ድምጽ ወሳኝ ይሆናል፡፡

4/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## የፌደራል የስፖርት ማህበራት አስተዳደር

## 10. የፌደራል ስፖርት ማህበር የቅድመ ምዝገባ መስፈርት

የፌደራል ስፖርት ማህበር እውቅና ለማግኘት የሚከተሉትን ማሟላት አለበት፡-

1/ ቢያንስ በ 7 ክልል የተመዘገቡና እውቅና ያገኙ የፌደራል ስፖርት ማህበራትን በአባልነት ያካተተ፤

2/ የፌደራል የስፖርት ማህበራትንና የሀገራችንን የስፖርት ህጎች ያከበረ የመተዳደሪያ ደንብ አዘጋጅቶ በጠቅላላ ጉባዔው የፀደቀ ሰነድ ማቅረብ፤

3/ በስፖርት ባህርያቸው ምክንያት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን ማሟላት የማይችሉ የፌደራል የስፖርት ማህበራት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገውን መስፈርት ማሟላት አለባቸው፡፡

4/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሰረት ተገቢውን መስፈርት ላሟላ የፌደራል ስፖርት ማህበር የእውቅና የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

5/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ንዑስ አንቀጽ (1) የተቀመጠው ድንጋጌ በባህል ስፖርት በተደራጀ የፌደራል የስፖርት ማህበራት ላይ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

## 11. የፌደራል የስፖርት ማህበራት ምዝገባ

1/ ማንኛውም የፌደራል የስፖርት ማህበር ከዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበር የአባልነት እውቅና ማግኘት ይኖርበታል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ የፌደራል ስፖርት ማህበራትን መቋቋም፣ ምዝገባ እና የአስተዳደር ስርዓት በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 12. የፌደራል ስፖርት ማህበር አቋም

1/ የፌደራል የስፖርት ማህበር አቋም በአለም አቀፍ የስፖርት ማህበር ህግ መሰረት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ የፌደራል ስፖርት ማህበር የምርጫ ሂደት እና የተመራጮች የስራ ዘመን ቆይታ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 13. የፌደራል ስፖርት ማህበር ተግባርና ኃላፊነት

የፌደራል ስፖርት ማህበር የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ በተሰማራበት የስፖርት ዓይነት ስፖርትን ያስፋፋል፤ ያለማል፣ የማህበረሰብ ስፖርት ይደግፋል፤

2/ ልዩ ተሰጥዖ ያላቸው ታዳጊ ወጣቶች በመመልመል ስልጠና ይሰጣል፤

3/ ደረጃቸውን የጠበቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ይገነባል፣ ያስፋፋል፤

4/ በተሰማራበት የስፖርት ዓይነት ለሚሰሩ የስፖርት ባለሙያዎች ተከታታይና ወቅታዊ የአቅም ግንባታ ተግባራትን ያከናውናል፤

5/ በተሰማራበት ስፖርት ዓይነት ለሚቋቋም ስፖርት ክለብ ዝርዝር የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤

6/ በፌደራል ስፖርት ማህበር የወጡ ህግጋትን ያከብራል፤

7/ የፀረ አበረታች ቅመሞች ህግን ያከብራል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፣ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ተገቢውን አሰራር ይዘረጋል፤

8/ በአለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ ስፖርታዊ ኩነቶች ሀገሪቱን ይወክላል፤

9/ ተግባራቱን ለማከናወን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፡፡

## 14. ስለክትትል እና ግምገማ

1/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር የስራ አፈፃፀምና የፋይናንስ አጠቃቀምን አስመልክቶ በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ የፌደራል ስፖርት ማህበራት ስራቸውን ህግን ተከትሎ ማከናወናቸውን ክትትል ያደርጋል፤

3/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ሚኒስቴሩ ለሚያከናውነው ክትትልና ቁጥጥር ተገቢውን መረጃ በመስጠት መተባበር ይኖርበታል፡፡

4/ ሚኒስቴሩ በክትትሉ ውጤት መሰረት ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሦስት

## ስለ ስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት

### 15. የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት ስለማቋቋም

1/ ማንኛውም ሰው ተገቢውን መስፈርት በማሟላት የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋምን ማቋቋም ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የሚቋቋም የማሰልጠኛ ተቋም በሚመለከተው የመንግስት ተቋም ህጋዊ ምዝገባና ዕውቅና ለማግኘት የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት ይኖርበታል፡-

ሀ) ህጋዊ የመመስረቻ ሰነድና የመተዳደሪያ ደንብ፣

ለ) በሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም የፀደቀ የማሰልጠኛ ማንዋል፣

ሐ) የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያላቸው ባለሙያዎችና አሰልጣኞች፣

መ) ስልጠና የሚሰጥበት የስፖርት ዓይነት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ፣ ቁሳቁስና ጽህፈት ቤት ያሟላ፣

ሠ) የአሠራር ሥርዓት እና ተቋማዊ አደረጃጀት ያለው፣

ረ) ህጋዊ የገቢ ምንጭ ያለው፣

3/ ሚኒስቴሩ ስለ ስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት ዝርዝር መስፈርትና የስልጠና ስርዓት መመሪያ ያወጣል፡፡

### 16. ስለ ስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት አቋም

1/ በፌደራል ደረጃ የሚቋቋሙ የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት እንደሚቋቋሙበት ደረጃና እንደሚሰጡት የስልጠና ዓይነት አደረጃጀት ይኖራቸዋል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋማት የሚከተሉት ጥቅል አደረጃጀቶች ይኖሯቸዋል፡-

ሀ) የአስተዳዳር ቦርድ፤

ለ) ዋና ስራ አስፈፃሚ፤ እና

መ) አስፈላጊ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

## 17. <u>የማሰልጠኛ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>

ማንኛውም የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋም የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ ተሰጥዖ ያላቸው ታዳጊዎችንና ወጣቶችን መልምሎ በመቀበል ያሰለጥናል፤ወደ ተለያዩ የስፖርት ክለቦች የሚሸጋገሩበትን የአሰራር መመሪያ በማውጣት ይተገብራል፤

2/ የሰልጣኞችን የምልመላ መስፈርቶች ያዘጋጃል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፤

3/ የአጫጭርና የመካከለኛ ወይም የረጅም ጊዜ ስልጠና ፕሮግራሞችን በመቅረፅ በተሰማራበት ዘርፍ ለሚሠሩ ባለሙያዎችና አመራሮች ስልጠና ይሰጣል፤

4/ አግባብነት ያላቸው ስልቶችን በመጠቀም የሰልጣኞቹን ብቃት ይመዝናል፤

5/ ለሚሰጠው ስልጠና አግባብነት ያለው የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

6/ የሀገር ውስጥ እና ውጭ ሀገር ሰልጣኞችን እና አትሌቶችን በህጋዊ መንገድ በመቀበል ስልጠና ይሰጣል፤

7/ የአሰልጣኞችና ሰልጣኞችን ስነ ምግባር ይከታተላል፤

8/ በአበረታች ቅመሞች ዙሪያ በየደረጃው ተከታታይ ስልጠና ይሰጣል፤

9/ ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፤ ሌሎች የገቢ ምንጮችን በመፍጠር ይተገብራል፤

10/ አላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል፤

11/ ተመሳሳይ ዓላማ ካላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ተቋማት ጋር ግንኙነት ይመሰርታል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>
## <u>የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር</u>

## 18. <u>የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች አስተዳደር</u>

1/ የስፖርት ማዘውተሪያ ያስገነባ ሰው ማዘውተሪያውን በባለይዞታነት ያስተዳድራል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ ዓለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን የሚያስተናግድ ማዘውተሪያ ሥፍራ እንዳስፈላጊነቱ ሊገነባ ይችላል፡፡

3/ በፌደራል ደረጃ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚለሙበት አግባብ እና የሚተዳደሩበት ሁኔታ በደንብ ይወሰናል፡፡

19. <u>የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች አመዳደብ</u>

1/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው መንግስታዊ ተቋም ጋር በመተባበር ስታንዳርድን ያዘጋጃል፤ የስፖርት ማዘወተሪያ ስፍራዎችን ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ ሦስት ይመድባል፡፡

2/ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ በተቀመጠለት ስንታንዳርድ መሠረት ለታቀደለት አገልግሎት ብቁ የሚያደርጉትን መሠረታዊ መሥፈርቶች የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

3/ አለም አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ለማስተናገድ ብቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ በደረጃ አንድ ይመደባል፡፡

4/ አገር አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ለማስተናገድ ብቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ በደረጃ ሁለት ይመደባል፡፡

5/ ክልል አቀፍ የስፖርት ውድድሮችን ለማስተናገድ ብቁ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ በደረጃ ሦስት ይመደባል፡፡

6/ ሚኒስቴሩ የማዘውተሪያ ስፍራዎችን የደረጃ ምደባ መዝገብ አደራጅቶ ይይዛል፣ ተደራሽ ያደርጋል፡፡

7/ ሚኒስቴሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የደረጃ ምደባ ስልጣኑን ለክልል በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

20. <u>ፈቃድ ስለመስጠት</u>

1/ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ የመሰናዶ ሥራ በደረጃ መሰረት ለማከናወን የሚፈልግ ማንኛውም ሰው፡-

ሀ) ሚኒስቴሩ በደረጃ አንድ ወይም ሁለት ለሚመደቡ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ፈቃድ ይሰጣል፤

ለ) አግባብነት ያለው የክልል አካል በደረጃ ሶስትና ለሌሎች የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራዎች ፈቃድ ይሰጣል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ እንዳስፈላጊነቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) ለተቀመጡት ደረጃዎች ፈቃድ በክልል እንዲሰጥ ሊወክል ይችላል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) (ሀ) መሰረት ተገቢው ፈቃድ ሳይኖረው የተገነባ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ አገር አቀፍና አለም አቀፍ ውድድሮችን እንዲያስተናግድ ሚኒስቴሩ ተገቢውን ቁጥጥር በማድረግ ማረጋገጫ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 21. ስለማመልከቻ አቀራረብ

1/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ማቋቋምና አገልግሎት መስጠት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ግንባታ ከመጀመሩ በፊት ፈቃድ እንዲሰጠው ለሚኒስቴሩ ወይም በህግ ስልጣን ላለው የክልል ተቋም ፈቃድ መጠየቅ አለበት፡፡

2/ አመልካቹ ከማመልከቻው ጋር ዝርዝር የመነሻ ሃሳብ፣ የማዘውተሪያ ስፍራውን ፕላን እና ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶችን አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

3/ አመልካቹ የመሰናዶ ስራውን ሲያጠናቅቅ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ማመልከት አለበት፡፡

## 22. ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለመስጠት

1/ ሚኒስቴሩ ወይም በህግ ስልጣን የተሰጠው የክልል አካል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራው ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ሲያምንበት ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የመሰናዶ ሥራ ለመጀመር የሚያስችል ፈቃድ ይሰጣል፡፡

ለ) አመልካቹ የመሰናዶ ሥራውን ሲያጠናቅቅ የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራው በፕላኑ መሠረት ደረጃውን ጠብቆ የተሰናዳ መሆኑን በማረጋገጠ ለአገልግሎቱ የተወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ለአመልካቹ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት በሚኒስቴሩ ለሚሰጥ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት አግባብ ባለው የክልል አካል ለሚሰጥ ፈቃድና የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚጠየቀው የአገልግሎት ክፍያ መጠን በክልሉ ይወሰናል፡፡

## 23. ስለስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አጠቃቀም

1/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ስፖርታዊ ኩነቶችን፣ በህግ እንዲከናወኑ ለተፈቀዱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኩነቶች ለማስተናገድ፣ የኦሎምፒክ መርሆችን በመከተል ለስፖርቱ ልማት የሚውሉ የተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራትን ለማከናወን ሊውሉ ይችላሉ፡፡

2/ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የገነባ የትምህርት ወይም ሌላ ተቋም ተገቢውን የአሠራር ሥርዓት በመዘርጋት ለማህበረሰቡ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ተገቢውን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ተመጣጣኝ ክፍያ ሊጠይቁ ይችላሉ፡፡

## 24. <u>የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከልሎ ስለመያዝ</u>

1/ ማንኛውም በህግ ስልጣን የተሰጠው ተቋም፡-

ሀ) ለስፖርት ማዘውተሪያነት የሚውሉ ስፍራዎችን በገጠር ቀበሌ እንደ ህዝቡ አሰፋፈር እና በከተማ መሪ ፕላን መሠረት ከልሎ መያዝ አለበት፤

ለ) እንደአካባቢው ሁኔታ በህብረተሰቡ የሚዘወተሩ የባህል ስፖርቶችን በማጥናት ለባህል ስፖርት ጨዋታዎች የሚያገለግሉ ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ከልሎ መያዝ ይኖርበታል፤

ሐ) በመሪ ፕላኑ ወይም እንደ ህዝቡ አሰፋፈር የተከለሉትን የማዘውተሪያ ስፍራዎች ከሚመለከተው አካል የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ መያዝ አለበት፡፡

2/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሠረት የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች በመሪ ማስተር ፕላን ወይም እንደ ህዝቡ አሰፋፈር ስለ መከለላቸው ይከታተላል፣ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

## 25. <u>የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችን ስለማልማት</u>

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 24 መሰረት የተከለለ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ እንደማዘውተሪያው ዓይነት የሚያስፈልጉ ደረጃቸውን ያሟሉ የስፖርት ቁሳቁሶችን አሟልቶ መገንባት አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ እና ተስማሚ መሆን አለበት፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## የአትሌቶች እና የስፖርት ባለሙያዎች አስተዳደር

## ንዑስ ክፍል አንድ
## የአትሌቶች አስተዳደር ሥርዓት

### 26. የአትሌቶች ምዝገባ

1/ ማንኛውም በአገርና በዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ኩነት የሚሳተፍ አትሌት በቅድሚያ በሚመለከተው ፌደራል ስፖርት ማህበር መመዝገብ አለበት፤

2/ የሚመለከተው ስፖርት ማህበር የአመዘጋገብ ስርዓት የሚመራበትን መመሪያ በማዘጋጀት ይተገብራል፤

3/ በዚህ አንቀፅ መሰረት ያልተመዘገበ አትሌት በማንኛውም አገር አቀፍ እና አገሪቱን በመወከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄድ ስፖርታዊ ኩነቶች ላይ መሳተፍ አይችልም፡፡

### 27. የአገር ውስጥ አትሌቶች ዝውውርና ቅጥር አስተዳደር

1/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር አትሌት እንደየዕድሜ ደረጃውና የስፖርት ዓይነት ስለሚቀጠርበትና ስለሚዛወርበት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

2/ የማንኛውም አትሌት የዝውውር ወይም የቅጥር የውል ስምምነት በሚመለከተው የፌደራል የስፖርት ማህበር መጽደቅ አለበት፤

### 28. የውጭ ሀገር አትሌቶችን ስለመቅጠር

1/ ማንኛውም የስፖርት ክለብ ከሚኒስቴሩ በሚያገኘው ፈቃድ መሰረት የውጭ ሀገር አትሌቶችን መቅጠር ይችላል፤

2/ የውጭ ሀገር አትሌቶች የክፍያ ስርዓትና የቅጥር መስፈርት ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይፈጸማል፡፡

3/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የተቀጣሪውን አትሌት የብቃት ማረጋገጫና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች አግባብነት ይመረምራል፣ የቅጥር ውሉን ያጸድቃል፡፡

4/ የውጭ አገር አትሌት በአገር ውስጥ ስፖርት ክለብ ተቀጥሮ መስራት የሚችለው በዚህ ስራ ህጋዊ ፈቃድ ባለው የንግድ ድርጅት አገናኝነት ነው፡፡

### 29. የአትሌት ማናጀር ወይም ተወካይ አስተዳደር

1/ ማንኛውም ማናጀር ወይም ተወካይ በዚህ ስራ ተገቢውን ህጋዊ ፈቃድ መያዝ ይኖርበታል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ የአትሌት ማናጀር ወይም ተወካይ ስለሚሰራበት ሁኔታ የአሰራር መመሪያ ከሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ጋር በመቀናጀት ያወጣል፡፡

3/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የአትሌት ማናጀር ወይም ተወካይ ከአትሌቱ ጋር የሚያደርገውን የአገልግሎት ውል ያጸድቃል፤

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ያጸደቀውን የአገልግሎት የውል ስምምነት ከእነዝርዝር ማብራሪያው ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት የሚወጣውን የመመሪያውን አፈጻጸም ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

30. <u>የአትሌት ማናጀር ወይም ተወካይ ኃላፊነት</u>

ማንኛውም የአትሌቶች ማናጀር ወይም ተወካይ የሚከተሉት ኃላፊነቶች ይኖሩታል፡-

1/ የአትሌቱን የስልጠና ሂደት በመደገፍ በተገቢው የውድድር ደረጃ እንዲሳተፍ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

2/ አትሌቱን በመወከል የውድድር ተሳትፎና የጥቅማ ጥቅም ውሎችን ይደራደራል፡፡

3/ የአትሌቱን የቅጥርና የዝውውር ስርዓት በመከታተል ያስፈጽማል፤

4/ የአትሌቱን ወቅታዊ ብቃት መሰረት በማድረግ የንግድ ተቋማት መልካም ስሙንና ዝናውን በመጠቀም የንግድ ተግባራት እንዲያከናውኑ ይደራደራል፤

5/ የአትሌቱን ደህንነት በስፖርታዊ ዝግጅትና ውድድር ወቅት ይከታተላል፤ ይጠብቃል፤

6/ በአበረታች ቅመሞች ዙሪያ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ የህግ ጥሰት እንዳይፈጸም ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፡፡

31. <u>የአትሌቶች መብትና ግዴታ</u>

1/ ማንኛውም አትሌት የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) በስፖርት ስልጠናና ውድድር ያለአድሎ የመሳተፍ፤

ለ) በሚሳተፉባቸው ስፖርታዊ ኩነቶች ላይ ግልፅና ፍትሃዊ መረጃ የማግኘት፤

ሐ) በስፖርት ማህበራት የመሳተፍ፣ የመምረጥና የመመረጥ፤

መ) ስልጠናውን የሚረዱ ግብዓቶች የማግኘትና የመጠቀም፤

ሠ) በሚሳተፉባቸው ስፖርቶች ጥቅም የማግኘት፣ ወይም ሲያሸንፍ እንደአግባብነቱ ሽልማትና ዕውቅና የማግኘት፤

ረ) በስልጠና ወይም በውድድር ወቅት ለሚያጋጥም ጉዳት ሙሉ የህክምና መድህን አገልግሎት የማግኘት፤

ሰ) በስፖርት ተሳትፎ ያገኘውን እውቅና ተጠቅሞ በህጋዊ መንገድ በስሙና ምስሉ ከሚገኘው የኢኮኖሚያዊና የሞራል መብት የማግኘት፤

2/ ማንኛውም አትሌት የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) በስፖርት ተሳትፎ የኩነቱን ህግና ደንብ ማክበር፤

ለ) የጸረ አበረታች ቅመሞችን ህግን ማክበር፤

ሐ) ስፖርታዊ ስነ ምግባሮችን ማክበር፤

መ) ወቅታዊ የጤና ምርመራ የማድረግ፤

ሠ) በአለም አቀፍ ስፖርታዊ ኩነቶች ሀገሪቱን በመወከል በፍጹም ትጋትና በተገቢው ስነ-ምግባር የማገልገል፤

ረ) ከስፖርት ኩነት በኂላ ስለውድድሩ ተገቢውን መረጃ የመስጠት፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የስፖርት ባለሙያዎች አስተዳደር ሥርዓት

### 32. የስፖርት ባለሙያዎች ምዝገባ፣

1/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ወይም የስፖርት ማሰልጠኛ ተቋም በዘርፉ የተሰማሩትን የስፖርት ባለሙያዎች ይመዘግባል፤ ለሚኒስቴር ያሳውቃል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ የባለሙያዎችን እና የሙያ ደረጃቸውን በስፖርት የመረጃ ቋት ያደራጃል፡፡

### 33. የስፖርት ባለሙያዎች ደረጃ አመዳደብ

ማንኛውም የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር በስፖርት ዓይነቱ ተገቢው የስልጠና፣ የትምህርት ደረጃና አግባብነት ያለው የስራ ልምድ መሰረት በማድረግ የስፖርት ባለሙያዎችን ደረጃ ይመድባል፤ አፈፃፀሙም በሚያወጣው በመመሪያ ይወሰናል፡፡

### 34. የውጭ አገር የስፖርት ባለሙያን ስለመቅጠር

1/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ወይም ክለብ፤ በሀገር ውስጥ በመስኩ ወቅታዊ ውጤት ያስመዘገበ ወይም ብቁ የሰለጠነ የሰው ኃይል አለመኖሩ ሲረጋገጥ የውጭ ሀገር የስፖርት ባለሙያ ሊቀጥር ይችላል፡፡

2/ የውጭ ሀገር የስፖርት ባለሙያዎች የክፍያ ስርዓትና የቅጥር መስፈርት ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ጋር በመተባበር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

3/ የውጭ አገር የስፖርት ባለሙያዎቹ የሀገሪቱን ባለሙያዎች የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት በመለየት ማብቃት ይኖርባቸዋል::

## ክፍል አምስት

## የስፖርት ኩነቶች አስተዳደርና የሽልማት አሰጣጥ ሥርዓት

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የስፖርት ኩነቶች አመራር ሥርዓት

**35. የስፖርት ኩነት ዓይነቶች**

1/ የአገሪቱ ብሔራዊ ቡድን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚካሄዱ ስፖርታዊ ኩነቶች ላይ አገሪቱን በመወከል ይሳተፋል፡፡

2/ ማንኛውም የስፖርት ክለብ የዓለም አቀፍ የክለቦች ሻምፒዮና ሊሳተፍ ይችላል፡፡

3/ አገር አቀፍ የስፖርታዊ ኩነቶች የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ) የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታ፤

ለ) አገር አቀፍ የሴቶች ጨዋታ፤

ሐ) አገር አቀፍ የታዳጊ ወጣቶች ስፖርት ስልጠና ፕሮግራም ምዘና ውድድር፤

መ) አገር አቀፍ ወጣቶች ኦሎምፒክ ጨዋታ፤

ሠ) አገር አቀፍ የተማሪዎች ጨዋታ፤

ረ) አገር አቀፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ስፖርት ፌስቲቫል፤

ሰ) አገር አቀፍ የባህል ስፖርት ፌስቲቫል፤

ሸ) አገር አቀፍ አርሶ አደርና አርብቶ አደሮች ስፖርት ፌስቲቫል፤

ቀ) አገር አቀፍ ሠራተኞች ፌስቲቫል፤

በ) አገር አቀፍ የስፖርት ሻምፒዮናዎች፤

ተ) የመከላከያ ወይም የፖሊስ ስፖርት ፌስቲቫል

ቸ) አገር አቀፍ የክለቦች ሻምፒዮና፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ሌሎች ስፖርታዊ ኩነቶችን በመቅረጽ ሊተገብር ይችላል፡፡

5/ ማንኛውም የስፖርት ንግድ ተቋም ወይም ስፖርታዊ ኩነቶችን በማዘጋጀት ሊተገብር ይችላል፡፡

6/ ሚኒስቴሩ በአገር አቀፍ ደረጃ የማህበረሰብ ስፖርት ተሳትፎን የሚያበረታቱ የስፖርታዊ ኩነቶችን በመቅረፅ ሊተገበር ይችላል፡፡

## 36. <u>የስፖርት ኩነቶችን ስለማዘጋጀት</u>

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት ስፖርታዊ ኩነቶችን የሚያዘጋጅ ማንኛውም ሰው ለስፖርት ዓይነቱ በፌደራል ስፖርት ማህበራት በወጡ ህጎች መሰረት አዘጋጅቶ መምራት ይኖርበታል፡፡

2/ የስፖርት ኩነትን የሚያዘጋጅ ማንኛውም ሰው ተሳታፊዎች ስለሚኖራቸው ተሳትፎ ተገቢውን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

3/ ማንኛውም ሰው በስፖርት ኩነት ዝግጅት ወቅት የአበረታች ቅመሞች ምርመራ ለማድረግ የሚያስችሉ አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎችን ማሟላት አለበት፡፡

4/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የስፖርት ኩነቶችን የማዘጋጀትና የመምራት ኃላፊነቱን ህጋዊ ፈቃድ ላላቸው ተቋማት በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

5/ በዚህ አንቀፅ መሠረት ለሚዘጋጁ የስፖርት ኩነቶች ዝግጅት ሚኒስቴሩ ተገቢውን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## 37. <u>አለም አቀፍ የስፖርት ኩነቶችን ስለማስተናገድ</u>

1/ ማንኛውንም ዓለም አቀፍ ስፖርታዊ ኩነትን በአገር ውስጥ ለማስተናገድ የሚፈልግ ሰው በቅድሚያ ለሚኒስቴሩ በማሳወቅ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ (1) መሰረት ፍቃድ ያገኘ የኩነት አዘጋጅ የመነሻ ሀሳቡን በማዘጋጀት ለሚመለከተው ዓለም አቀፍ ስፖርት ማህበር በመላክ ማረጋገጫ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

## 38. <u>አገር አቀፍ የስፖርት ኩነቶችን ስለማስተናገድ</u>

1/ ማንኛውም አገር አቀፍ የስፖርት ኩነትን የሚያዘጋጅ ሰው በቅድሚያ ኩነቱ የሚስተናገድበትን ክልል የሚለይበትን መስፈርት ያዘጋጃል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተመረጠው ክልል ኩነቱን ለማስተናገድ ፍቃደኝነቱን መግለጽ ይኖርበታል፡፡

3/ ሚኒስቴሩ አገር አቀፍ የስፖርት ኩነቶች ስለሚስተናገዱበት አግባብ ተገቢውን የድጋፍና የክትትል ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 39. በስፖርት ኩነቶች ተሳትፎ ስለማድረግ

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት የተመዘገበ ማንኛውም አትሌት ወይም አሰልጣኝ ወይም ክለብ፣ በአገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ የስፖርት ኩነቶች ላይ ፡ ተሳትፎ ሊያደርግ ይችላል፡፡

2/ ማንኛውም የውጭ አገር አትሌት፣ አሰልጣኝ፣ ክለብ፣ ቡድን ወይም የልዑካን ቡድን በሀገር ውስጥ በሚደረጉ የስፖርት ኩነቶች ላይ ለመሳተፍ በቅድሚያ ከላኪው አገር እና ከሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ተገቢውን ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ፍቃዱን የሰጠው የፌደራል ስፖርት ማህበር ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡት የኩነት ተሳታፊዎች ትክክለኛ መረጃ ለሚኒስቴሩ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

## 40. ለስፖርት ኩነቶች ስለሚደረጉ የውጭ ሀገር ጉዞዎች

1/ ማንኛውም በዓለም አቀፍ ስፖርት ኩነት ላይ ለመሳተፍ ወደ ውጭ አገር የሚንቀሳቀስ አካል በቅድሚያ ከሚኒስቴሩ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ለሚንቀሳቀሱ አካላት ሚኒስቴሩ ተገቢውን ድጋፍ፣ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

## 41. የስፖርት ኩነቶችን ስለማገድ

በዜጎች ደህንነት፣ ሰላም እና ጤና ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያስከትል ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት ወይም እንደሚከሰት ሲታመን ማንኛውንም የስፖርት ኩነት እንዳይካሄድ ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ሪፖርት ሲደርሰው ሚኒስቴሩ ሊያግድ ይችላል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት
## የብሔራዊ ቡድን ዝግጅት

### 42. ብሔራዊ ቡድን ስለማቋቋም

1/ የፌደራል የስፖርት ማህበር በተደራጀበት የስፖርት ዓይነት የብሔራዊ ቡድን ማቋቋም አለበት፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚቋቋመው ብሔራዊ ቡድን ሀገሪቱን የሚወክል ደረጃውን የጠበቀ ስያሜ፣ ትጥቅ፣ አርማና ስነ-ምግባር ሊኖረው ይገባል፤ ዝርዝሩ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

### 43. የብሔራዊ ቡድን ምልመላ

1/ ማንኛውም በብሔራዊ ቡድን የሚሳተፍ አትሌት በአገር ወይም በዓለም አቀፍ ውድድሮች ላይ በሚያስመዘግበው ወቅታዊ ውጤት እና ብቃት መሰረት ይመለመላል፡፡

2/ ማንኛውም የስፖርት ክለብ ለብሔራዊ ቡድን የተመረጠን አትሌት በተጠየቀ ጊዜ መላክ አለበት፡፡

3/ የፌደራል ስፖርት ማህበር በብሄራዊ ቡድን አባልነት የሚመለምለውን አትሌት ከአበረታች ቅመሞች ነጻ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

4/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ስለአትሌት አመራረጥ ተገቢውን መስፈርት ያዘጋጃል፤ ሂደቱንና የተመረጠ አትሌትን በሚመለከት ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

5/ በዚህ አንቀጽ አፈፃፀም ላይ ቅር የተሰኘ አትሌት በዚህ አዋጅ በተቋቋመው የግጭት አፈታት ስርዓት መሰረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

### 44. የብሄራዊ ቡድን አሰልጣኞች ምደባ

1/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ግልፅ ውድድር በማካሄድ ባስመዘገቡት ውጤት የብሔራዊ ቡድን አሰልጣኞችን ይመድባል፣ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አፈፃፀሙ ላይ ቅር የተሰኘ አሰልጣኝ በዚህ አዋጅ በተቋቋመው የግጭት አፈታት ስርዓት መሰረት ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

### 45. የብሔራዊ ቡድን ዝግጅት

1/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር ብሔራዊ ቡድኑን በዝግጅትና ውድድር ወቅት የሚመራና የሚያስተባብር አካል ይመድባል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ ለተመረጡ ብሄራዊ ስፖርታዊ ውድድሮች የበጀት ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፤ የውድድሩን ሂደት ይከታተላል፤ ዝርዝሩ በመመሪያ ይወሰናል፤

3/ ሚኒስቴሩ የብሔራዊ ቡድኑን ዝግጅትና ውድድር የሚከታተል፣ የሚደግፍና የሚቆጣጠር አካል ያደራጃል፡፡

## 46. የብሔራዊ ቡድን የተሳትፎ ሥነ-ሥርዓት

1/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው መንግሥታዊ አካል ጋር በመቀናጀት ለተሳትፎ የሚንቀሳቀሰውን ብሔራዊ ቡድን ቃለ-መሐላ በማስገባት የሽኝት መርሃ-ግብር ይፈጽማል፤ አጠናቆ ሲመለስ ተገቢውን አቀባበል ያደርጋል፡፡

2/ ብሔራዊ ቡድኑ ዓለም አቀፍ ውድድሮች በመሳተፍ ሀገሪቱን በተገቢው ክብርና ሙያዊ ስነ-ምግባር ይወክላል፡፡

3/ በብሔራዊ ቡድን የሚሳተፍ አትሌት ወይም የስፖርት ባለሙያ በውድድር ወቅትና በብሔራዊ ቡድን ቆይታዎች ከማንኛውም የሀገርን ገፅታ ከሚያጎድፉ ተግባራት መቆጠብ አለበት፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ አትሌት ወይም የስፖርት ባለሙያ ከማንኛውም ቀጣይ የብሔራዊ ቡድን ተሳትፎ ይሰናበታል፡፡

# ንዑስ ክፍል ሦስት
# የስፖርት ሽልማት አሰጣጥ ሥርዓት

## 47. የስፖርት ሽልማት አሰጣጥ

1/ አገሪቱን በመወከል በአለም አቀፍ ውድድሮች ላይ ውጤት ላስመዘገቡ አትሌቶች፣ የስፖርት ባለሙያዎችና የብሔራዊ ቡድን አባላት እንደ ውድድሩ ደረጃና እንደተሳትፎው መጠን ሽልማትና እውቅና ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ የአገሪቱን የስፖርት እድገት በዕውቀት፣ በችሎታ እና በሀብት በመደገፍ የላቀ አስተዋጽዎ ላበረከቱ ወይም ረጅም ዘመን ላገለገሉ ግለሰቦች ሽልማት ይሰጣል፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሠረት የሚሰጠው ሽልማት እንደ አግባብነቱ በዓይነትና በገንዘብ ወይም ልዩ ሀገራዊ ሽልማት እና የምስክር ወረቀት ሊሆን ይችላል፤ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ስለስፖርት ፋይናንስ አስተዳደር

### ንዑስ ክፍል አንድ

### የስፖርት ኢንቨስትመንት

**48. ስለስፖርት ኢንቨስትመንት**

በህግ ስልጣን የተሰጠው የመንግስት ተቋም የስፖርት ኢንቨስትመንት እንዲስፋፋ ተገቢውን የአሰራር ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡

**49. የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ማረጋገጫ**

1/ ሚኒስቴሩ በሀገር ውስጥ የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ለሚያመርቱ እና ከውጭ ሀገር ለሚያስገቡ ተቋማት ተገቢውን መስፈርት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማዘጋጀት የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ለሚሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ተገቢውን የአሠራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

**50. የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ማበረታቻ ሥርዓት**

1/ ሚኒስቴሩ በሀገር ውስጥ የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ለሚያመርቱ አካላት ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር በመተባበር የማበረታቻ ሥርዓት ይዘረጋል፡

2/ ሚኒስቴሩ ከውጭ ሀገር በድጋፍ ወይም ከቀረጥ ነፃ በሚገቡ የስፖርት ትጥቅና መሳሪያዎች ተገቢውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡

**51. የስፖርት ንግድ**

1/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር የስፖርት ነክ ንግድ እንዲስፋፋ ተገቢውን አሰራር ይዘረጋል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ የስፖርት ውርርድ በሀገሪቱ ውስጥ ስለሚተዳደርበት ስርአት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

### ንዑስ ክፍል ሁለት

### የፌደራል ስፖርት ማህበራት የፋይናንስ አስተዳደር

**52. የፌደራል የስፖርት ማህበር የገቢ ምንጭ**

1/ ማንኛውም የፌደራል የስፖርት ማህበር ከሚከተሉት ምንጮች ገቢ ሊሰበስብ ይችላል፣

ሀ) ከፌደራል ማህበር የሚሰጣቸው የፋይናንስ ድጋፎች፣

ለ) ከውድድር ትኬት እና ከስፖርታዊ ኩነቶች ሽያጭ፣

ሐ) ከስፖርት ክለቦች የሚሰበሰብ መዋጮ፣

መ) ከአትሌት ዝውውር የሚገኝ፣

ሠ) ከሚዲያ ሽፋንና ከማስታወቂያ ስራ የሚገኝ፣

ረ) ከሚሰጡት አገልግሎት የሚሰበሰብ፣

ሰ) ከተለያዩ ከስፖርት ነክ ንግዶች የሚገኝ፤

ሸ) ከስፖንሰርሺፕ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ መንግስት ሀገሪቱ ውጤት በማስመዝገብ የምትታወቅባቸውን ስፖርቶችና ሀገራዊ እምቅ የስፖርት ሀብትን በመለየት እንዳግባብነቱ ድጋፍ ሊያደርግ ይችላል፤ አፈፃፀሙ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## 53. <u>የፌደራል ስፖርት ማህበራት የፋይናንስ አጠቃቀም ሥርዓት</u>

1/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት የሚያገኟቸውን ገቢዎች ተገቢውን የፋይናንስ ስርዓት በመከተል ለታለመለት ዓላማ ብቻ መጠቀም ይኖርባቸዋል፡፡

2/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት ሀገር ውስጥ በሚገኙ ባንኮች የሂሳብ ቁጥር ከፍተው ያንቀሳቅሳሉ፤ እንደ አስፈላጊነቱ በብሔራዊ ባንክ ፈቃድ በውጭ ሀገር ባንኮች ጊዜያዊ የሒሳብ ቁጥር ሊከፍቱ ይችላሉ፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (2) መሰረት በውጭ አገር ባንክ የሂሳብ ቁጥር ሊከፈት የሚችለው አገሪቱን በመወከል በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚዘጋጁ በስፖርታዊ ውድድሮች ወቅት ብቻ ይሆናል፡፡

4/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት የፋይናንስ አጠቃቀማቸውን በየወቅቱ ተከታትለው በሚመለከተው ህጋዊ አካል ማስመርመር አለባቸው፡፡

5/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት የሒሳብ ምርመራ ሪፖርቱን ለሚኒስቴሩ በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሪፖርት ማድረግ አለባቸው፡፡

6/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5) መሰረት ተገቢውን የሒሳብ ሪፖርት በወቅቱ ያላቀረበ የፌደራል ስፖርት ማህበር አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

7/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት በዚህ አዋጅ አንቀፅ 52 ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ከመንግስት የሚሰጣቸውን የፋይናንስ ድጋፍ በመንግስት የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር ህጎች መሰረት መጠቀም አለባቸው፡፡

54. <u>የፋይናንስ አጠቃቀም ክትትልና ድጋፍ</u>

1/ ሚኒስቴሩ የፌደራል ስፖርት ማህበራት ያገኟቸውን ገቢዎች አጠቃቀም ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ተገቢውን እርምጃ ይወስዳል፡፡

2/ የፌደራል ስፖርት ማህበራት፣ ገቢያቸውን ስለሚሰበሰቡበትና ስለሚጠቀሙበት አግባብ መመሪያ በማዘጋጀት በጠቅላላ ጉባኤ ማጸደቅ አለባቸው፡፡

55. <u>የክትትልና ቁጥጥር ኃላፊነት</u>

1/ ማንኛውም የፌደራል የስፖርት ማህበር፣

ሀ) የስፖርት ክለቦች ለአሰልጣኞችና ለአትሌቶች የሚከፍሉት ክፍያ ግልፅና ተመጣጣኝ ዋጋ መፈጸሙን መቆጣጠርና መከታተል አለባቸው፡፡

ለ) ክለቦች ዘላቂ ሕልውናቸውን አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ ከገቢያቸው በላይ ወጪ እንዳያወጡ መከታተል አለባቸው፡፡

ሐ) ክለቦች በየዓመቱ ሂሳባቸውን በውጪ ኦዲተር ማስመርመራቸውን መቆጣጠር አለባቸው፡፡

2/ ማንኛውም ክለብ አገር አቀፍ ስፖርት ማህበሩ የሚያወጣውን ህግና መመሪያን አክብሮ መንቀሳቀስ አለበት፡፡

3/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር በዚህ አንቀጽ የተገለጹትን ግዴታዎች ተላልፎ በተገኘ የስፖርት ክለብ ላይ ተገቢውን አስተዳደራዊ እርምጃ መውሰድ ይኖርበታል፤

## <u>ንዑስ ክፍል ሶስት</u>

## <u>የፌደራል ስፖርት ልማት ፈንድ</u>

56. <u>መቋቋም</u>

1/ የፌደራል ስፖርት ልማት ፈንድ ከዚህ በኃላ "ፈንድ" እየተባለ የሚጠራ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ ስለፈንዱ የገቢ ምንጭ፣ ስለገቢ አሰባሰብና አከፋፈል፣ ስለ ድጋፍ መስክ እና ስለፈንዱ አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሰባት

## የስፖርት ግጭት አፈታት ሥርዓት

### 57. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ ስለማቋቋም

1/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር በተሰማራበት የስፖርት ዓይነት የሚነሱ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን የሚፈታ ኮሚቴ ማዋቀር አለበት፡፡

2/ የኮሚቴው አባላትና አወቃቀር በፌደራል ስፖርት ማህበር እንደ አግባብነቱ ይወሰናል፡፡

3/ የሚመለከተው የፌደራል ስፖርት ማህበር የኮሚቴው አባላት የስራ ዘመን እና ስለሚመራበት ሁኔታ የአሰራር ሥርዓት ይወስናል፡፡

### 58. በኮሚቴው ስለሚታዩ ጉዳዮች

1/ ኮሚቴው በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ተቀብሎ በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡-

ሀ) የፌደራል ስፖርት ማህበራት የአመራሮች ምርጫ አፈጻጸም፣

ለ) የኩነቶች ዝግጅት አመራር፣

ሐ) የፌደራል ስፖርት ማህበራት የሀብት አሰባሰብና አጠቃቀም፣

መ) የአትሌቶችና የስፖርት ባለሙያዎች ምልመላና መረጣ፣

ሠ) የአትሌቶችና የስፖርት ባለሙያዎች ቅጥርና ዝውውር አግባብነት፣

ረ) የሜዳ መግቢያ ትኬት ሽያጭ፣

ሰ) የዳኝነት አገልግሎት አሰጣጥ፣

ሸ) ትንኮሳና አድሎአዊነት፣

ቀ) የአትሌቶች ምዝገባ

2/ ኮሚቴው በማህበሩ በሚደረጉ ስፖርታዊ ኩነቶች ላይ ጊዜያዊ ጽሕፈት ቤትን በማቋቋም በወቅቱ የሚነሱና አስቸኳይ ውሳኔ የሚሹ ቅሬታና አቤቱታዎችን በመመርመር ውሳኔ ይሰጣል፡፡

3/ ኮሚቴው በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (1) የቀረቡለትን አቤቱታዎች ከቀረበለት ቀን አንስቶ ባሉት በ10 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4/ በኮሚቴው ስልጣን ስር የማይወድቁ ስፖርታዊ አለመግባባቶችን ተቀብሎ ውሳኔ የሚሰጥ የስፖርት ግልግል ጉባኤ ይቋቋማል፤ ዝርዝሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

59. ይግባኝ ስለማቅረብ

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ (3) ወይም (4) መሰረት በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ውሳኔ ከተሰጠው ቀን አንስቶ ባሉት 30 የስራ ቀናት ይግባኝ አቤቱታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፤ ሆኖም የፍርድ ቤቱ ውሳኔ የህግ ስህተት አለበት ብሎ የሚከራከር ወገን የፍርድ ቤቱ ውሳኔ በደረሰው በ60 ቀን ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት
## መረጃ ሥርዓት

60. የስፖርት መረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ሥርዓት

1/ አገራዊ የስፖርት ሀብቶች በአግባቡ ተመዝግበው በመረጃ ቋት መያዝ አለባቸው፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት የሚደራጀው የመረጃ ቋት በሀገሪቱ እንቅስቃሴ የሚደረግባቸው የስፖርት ዓይነቶች፣ አትሌቶች፣ የስፖርት ባለሙያዎች፣ ክለቦች፣ የስፖርት ማህበራት፣ የማሰልጠኛ ተቋማትን ፣የስፖርት ማዘውተሪያዎችንና የሀገራችን የተሳትፎ ታሪካዊ መረጃዎችና ውጤቶችን መያዝ አለበት፡፡

3/ ሚኒስቴሩ የሀገሪቱን የስፖርት የመረጃ ቋት በዘመናዊ መልክ ያደራጃል፤ በየጊዜው መረጃውን ወቅታዊ ያደርጋል፣ ለማህበረሰቡ በተለያዩ ዘመናዊ ዘዴዎች ተደራሽ ያደርጋል፡፡

4/ ሚኒስቴሩ ከሚመለከተው አካል ጋር በመተባበር የአገሪቱን ታሪካዊ የስፖርት ሀብቶችን በማሰባሰብ በአውደ-ርዕይ ለህዝብ ተደራሽ የሚያደርግ የስፖርት ቤተ-መዘክር ሊያቋቁም ይችላል፡፡

61. መረጃ የመያዝ ኃላፊነት

1/ ማንኛውም የፌደራል ስፖርት ማህበር ስለሚያስተዳድረው ፕሮጀክትና ፕሮግራም ዝርዝር መረጃ መያዝ አለበት፡፡

2/ የፌደራል ስፖርት ማህበር የያዘውን መረጃ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለህዝብ ተደራሽ ማድረግ አለበት፡፡

## 62. የመረጃ ስርጭትና አጠቃቀም ሥርዓት

1/ የፌደራል ስፖርት ማህበር የብሔራዊ ቡድን አትሌትና አሰልጣኝ ምርጫና ዝግጅትን በተመለከተ ግልፅ መረጃ ለህብረተሰቡ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡

2/ ማንኛውም የስፖርት ተቋማት ግልጽና ትክክለኛ መረጃ ለመገናኛ ብዙሃን መስጠት አለበት፡፡

3/ የመገናኛ ብዙሃን የስፖርት ኩነት ዝግጅትና አፈጻጸም እንዲሁም አገራዊ የስፖርት ልማት ላይ ግልጽና ትክክለኛ መረጃ ለህብረሰተሰቡ ማድረስ አለባቸው፡፡

# ክፍል ዘጠኝ

# የተከለከሉ ተግባራት እና ቅጣት

## 63. በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ የተከለከሉ ተግባራት

በስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች የሚከተሉትን መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡

1/ በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም በስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ ውስጥ ሁከት ሊያስነሳ የሚችል ድርጊት መፈጽም፤

2/ በስፖርት ማዘውተሪያ ውስጥ ማናቸውንም አይነት በቃል፣ በዜማ፣ በጽሑፍ፣ በምልክት እና በአለባበስ የሚገለፁ መልካም ስነ ምግባርን የሚፃረሩና ሁከትን ሊያነሳሱ የሚችሉ ድርጊቶች መፈፀም፤

3/ የዘረኝነት እና የማህበራዊ ልዩነትን የሚያንፀባርቁ ማናቸውንም ዓይነት ድርጊቶች መፈፀም፤

4/ ስፖርታዊ እንቅስቃሴዎች ከመጀመራቸው በፊት ወይም በሚካሄዱበት ወቅት ማንኛውንም አይነት የፖለቲካ ወይም ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎችን ማካሄድ፤

5/ በሰው ጤና፣ አካል ወይም ስነ-ልቦና ላይ ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ ስለታማ መሳሪያዎችን፣ የተለያዩ የሚተኮሱ፣ የሚወረወሩ፣ የሚፈነዱ፣ የሚቀጣጠሉ ወይም መርዛማ ቁሳቁሶችን ይዞ መግባት፤

## 64. ስለአበረታች ቅመሞች

1/ ማንኛውም አትሌት በስፖርት አካላዊና ስነ ልቦናዊ የበላይነትን ለማግኘት በማሰብ በዓለም አቀፍ ፀረ አበረታች ቅመሞች ህግ የተከለከሉ አበረታች ቅመሞችን መጠቀም የተከለከለ ነው፡፡

2/ ማንኛውም ሰው ለአትሌት አበረታች ቅመሞችን እንዲጠቀም ማዘዝ ወይም መስጠት ወይም መጠየቅ ወይም ማመቻቸት ወይም ማስገደድ የተከለከለ ነው፡፡

3/ ማንኛውም ሰው ለፀረ አበረታች ቅመሞች መከላከል ለሚደረግ የቁጥጥርና የምርመራ ተግባር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

4/ አበረታች ቅመሞችን ያለፈቃድ ወደ አገር ውስጥ ማስገባት፣ ማምረት ፣መሸጥ ፣ ማከፋፈል፣ ማዘዋወር ወይም ይዞ መገኘት የተከለከለ ነው፡፡

## 65. ስፖርታዊ ማጭበርበር

1/ ለፌደራል ስፖርት ማህበር አመራር ወይም አባል ሆኖ ለመመረጥ በማሰብ፣ ለተለያዩ አካላት የገንዘብ ወይም የተለያዩ ስጦታዎችን በመስጠት ማባበል የተከለከለ ነው፡፡

2/ ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የማንኛውም የስፖርት ውድድሮች ወይም ኩነት ውጤትን ለማስቀየር ለአትሌት፣ ለዳኛ፣ ለአሰልጣኝ፣ ለቡድን መሪ ወይም ለሌሎች ሰዎች ገንዘብ መስጠት፣ መቀበል፣ ማስገደድ፣ ድርድር ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

## 66. አስተዳደራዊ እርምጃዎች

1/ ሚኒስቴሩ ይህንን አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ህጎች የተደነገጉ ጥፋቶችን በፈፀመ አካል ላይ በዚህ አንቀጽ ሥር የተዘረዘሩት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

2/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ሰው ቀላል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 ንዑስ ቁጥር 1 በመተላለፍ የስራ አፈፃፀምና የፋይናንስ አጠቃቀምን አስመልክቶ በየሩብ ዓመቱ ለሚኒስቴሩ ሪፖርት ያላቀረበ፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 ንዑስ ቁጥር 3 በመተላለፍ ሚኒስቴሩ ለሚያከናውነው ክትትልና ቁጥጥር ተገቢውን መረጃ በመስጠት ያልተባበረ፤

ሐ/ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው መመሪያ መሰረት ዓመታዊ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ያላካሄደ፤

መ/ በዚህ አዋጅ መሰረት በሚወጣው መመሪያ የተደነገገውን የፌደራል ስፖርት ማህበራት የስብሰባ ስነ ስርዓት ያላከበረ፤

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 61 ንዑስ ቁጥር 1 በመተላለፍ የፌደራል ስፖርት ማህበር ስለሚያስተዳድረው ፕሮጀክትና ፕሮግራም ዝርዝር መረጃ ያልያዘ፤

3/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ሰው ከባድ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 20 በመተላለፍ የማዘውተሪያ ስፍራ ፈቃድ ሳይኖረው የማዘውተሪያ ስፍራ የገነባ፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 22 በመተላለፍ የብቃት ማረጋገጫ ሳይኖረው የማዘውተሪያ ስፍራን ለአገልግሎት ያዋለ፤

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 በመተላለፍ የማዘውተሪያ ስፍራን በህግ ላልተፈቀደ አገልግሎት ያዋለ፤

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 ንዑስ ቁጥር 4 በመተላለፍ ያጸደቀውን የውጭ ሀገር አትሌት የአገልግሎት የውል ስምምነት ከእነዝርዝር ማብራሪያው ለሚኒስቴሩ ያላሳወቀ፤

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39 (3) በመተላለፍ ወደ አገር ውስጥ ስለሚገቡት የኩነት ተሳታፊ የውጭ ሀገር ዜጎች ትክክለኛ መረጃ ለሚኒስቴሩ ያላሳወቀ፤

ረ/ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሰረት የምዝገባ የምስክር ወረቀት ወይም የፈቃድ እድሳት ሳይኖረው በየትኛውም የስፖርት ማህበር ስም የተንቀሳቀሰ ወይም ስፖርታዊ ኩነት ላይ የተሳተፈ ወይም ያዘጋጀ፤

ሰ/ ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሰረት በፌደራል ስፖርት ማህበር ቦርድ አባልነት ወይም በስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልነት መሥራት የማይችል ሰው አካቶ ከተገኘ፤

ሸ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 ንዑስ ቁጥር 1 በመተላለፍ የፌደራል ስፖርት ማህበር የሰበሰበውን ገቢ ከታለመለት ዓላማ ውጪ የተጠቀመ እንደሆነ፤

ቀ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተጠቀሰ ቀላል የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጥ ጥፋትን በተደጋጋሚ ጊዜ ከፈፀመ፡፡

4/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን የፈፀመ ሰው በገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 30 ንዑስ ቁጥር 6 የተገነገገውን በመተላለፍ ተገቢውን ክትትል ባለማድረግ አትሌቱ ለአበረታች ቅመሞች የህግ ጥሰት የተጋለጠ እንደሆ ከ100,000 - 200,000 ሺህ (ከመቶ ሺህ እስከ ሁለት መቶ ሺህ) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

ለ) በዚህ አዋጅ አንቀፅ 40 ንዑስ ቁጥር 1 በመተላለፍ ህጋዊ አሰራርን ያልተከተለ ወይም በህጋዊ አሰራር ሽፋን አላማውን የሳተ የውጪ ግንኙነት ወይም ጉዞ የፈጸመ 100,000 ብር (አንድ መቶ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 43 ንዑስ (2) በመተላለፍ ለብሔራዊ ቡድን የተመረጠን አትሌት በወቅቱ ያልላከ የስፖርት ክለብ 75,000 ብር (ሰባ አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46 ንዑስ ቁጥር 3 በመተላለፍ የሀገርን ስም ወይም ገፅታ የሚያጠፋ ተግባራት የፈፀመ አትሌት ወይም የስፖርት ባለሙያ በቅድሚያ በ75,000 ብር (ሰባ አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

ሠ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 53 ንዑስ ቁጥር 4 በመተላለፍ ያገኘውን ገቢ በህጋዊ ኦዲተር ያላስመረመረ የፌደራል ስፖርት ማህበር 75,000 ብር (ሰባ አምስት ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

5/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) መሰረት በሚሰጠው ማስጠንቀቂያ የተፈፀመውን ጥፋት፣ ጥፋቱ የሚታረምበትን ጊዜና አግባብ እንዲሁም ከጥፋቱ ካልታረመ በቀጣይ የሚወሰድበትን እርምጃ በግልጽ በመጥቀስ በጽሁፍ መስጠት አለበት፡፡

6/ ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ስር የተጠቀሱትን ጥፋቶች ከሁለት ጊዜ በላይ የፈፀመን ሰው እስከ ስድስት ወር ለሚደርስ ጊዜ ሊያግድ ይችላል፡፡

7/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) መሰረት የሚወሰድ የእግድ እርምጃ የተፈፀመውን የሕግ ጥሰት፣ እግዱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ እና ሊደረግ የሚገባውን ማስተካከያ በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ በፅሁፍ መሰጠት አለበት።

8/ ከሚከተሉት ጥፋቶች አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ጥፋቶችን የፈፀመ ሰው እንዲሰረዝ ይደረጋል፡-

ሀ) ከሶስት ጊዜ በላይ ተደጋጋሚ የእግድ እርምጃ የተወሰደበት ሲሆን፤

ለ) የሀገራችንን ብሔራዊ ጥቅም በሚጎዳና በወንጀል በሚያስጠይቅ አደገኛ ተግባራት ላይ የተሰማራ እንደሆነ፤

ሐ) ይህን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣ ደንብና መመሪያ መሰረት የሚያሰርዝ ድርጊት ላይ የተሰማራ እንደሆነ፤

9/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8) መሰረት የሚወሰድ የመሰረዝ እርምጃ የተፈፀመውን ጥፋት፣ እርምጃውን ለመውሰድ መነሻ የተደረገ የሕግ መሰረት እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎች በግልጽ በሚያሳይ ሁኔታ በፅሁፍ መሰጠት አለበት።

## 67. ቅጣት

ማንኛውም ሰው፡-

1/ ከአንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (3) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ አግባብበነት ባለው የወንጀል ህግ ድንጋጌ መሰረት ይቀጣል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 63 በንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ሰው እንደነገሩ አግባብነት እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት እና እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 63 ንዑስ አንቀፅ (5) የተደነገገውን በመተላለፍ ወንጀል የፈጸመ ማንኛውም ሰው እንደነገሩ ሁኔታ እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

4/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 64 ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም አትሌት ከሶስት ዓመት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና ከአንድ መቶ ሺህ ብር እስከ ሦስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

5/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 64 ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው እንደነገሩ ሁኔት እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እና እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

6/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 64 ንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው ሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም እስከ አንድ መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

7/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 64 ንዑስ አንቀጽ (4) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ ማንኛውም ሰው እስከ ሰባት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራትና እስከ አምስት መቶ ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

8/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 65 ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

9/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 65 ንዑስ አንቀጽ (2) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ማንኛውም ሰው አስር ዓመት በማያንስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

## ክፍል አስር
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 68. ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2/ ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

### 69. የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1/ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎች አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 729/2004 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2/ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ደንብ፣መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

### 70. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዲስ አበባ ……. ቀን 2018 ዓ.ም
ታዬ አፅቀስላሴ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት